የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ህዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 5
ADDIS ABABA 3rd December, 2012

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፯፻፸/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለደሴ-ኩታበር-ተንታ መገንጠያ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............ ................ገጽ ፮ሺ፮፻፷፭

**CONTENTS**

Proclamation No. 770/2012

Kuwait Fund for Arab Economic Development Loan Agreement for Financing the Dessie-Kutaber-Tenta Junction Road Project Ratification Proclamation ....... Page 6665

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፸/፪ሺ፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለደሴ-ኩታበር-ተንታ መገንጠያ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፰ ሚሊዮን (ስምንት ሚሊዮን) የኩዌት ዲናር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ጁላይ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፲፫ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION No. 770/2012.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE KUWAIT FUND FOR ARAB ECONOMIC DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development stipulating that the Kuwait Fund for Arab Economic Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of KD 8,000,000 (Eight Million Kuwait Dinars) for financing the Dessie-Kutaber-Tenta Junction Road Project was signed in Addis Ababa on the 15th day of July 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 22nd day of November 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

| ያንዱ ዋጋ Unit Price | 2.30 |
| --- | --- |

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለደሴ-ኩታበር-ተንታ መገንጠያ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፸/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Kuwait Fund for Arab Economic Development Loan Agreement for Financing the Dessie-Kutaber-Tenta Junction Road Project Ratification Proclamation No.770/2012".

፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement, signed in Addis Ababa on the 15th day of July 2012, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development is hereby ratified.

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፰ ሚሊዮን /ስምንት ሚሊዮን/ የኩዌት ዲናር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of KD 8,000,000 (Eight Million Kuwait Dinars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ህዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of December, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት